## <u>መዘክር</u>

### <u>የቱ ነው</u>

ራስህን ጠይቅ።
የቱ ነው ደጉ ምግባረ መልካም
በሥራ ማመን መቆም ለሰላም፣
ወይስ ችላ ባይነት ባለመስማማት
ያለመዋደድ ሁሌ መጣላት፣
እርቅ ያለመሻት ማወነባበድ
መታመን አጥቶ ሁሌ መርበድበድ።

ወይስ በመፈቃቀድ በመፈቃቀር
ዕውን በማድረግ ሕይወትን መፍጠር
ሃይማኖት ጸንቶ ባሕልን ማክበር፣
ወይስ ለግል ጥቅም ራስን መሸጥ
በገንዘብ ምርኮ አገር መለወጥ፣
ወይስ ሳይጠላሉ በመተሳሰር
አገር መገንባት በመተባበር
ሳይለያዩ በመከባበር።

የትኛው ነው ኃጢአቱ
መብት ነፃነት ማጎናጸፉ
ድሎት ብልጽግና ማትረፍረፉ፣
ሕዝብ ለሕዝብ እንዲገበያይ
በነፃ ወጥቶ ምርቱን እንዲያሳይ፣
ሕግና ፍትህ እንዳይጓደል
አቅም የሌለው እንዳይበደል፣
ዕውቀት ያለውም እንዳይገታ
ባለው ችሎታ እንዲበረታ፣
ሰዉ ባሻው ተዘዋውሮ
ብሔራዊ መብቱ ተከብሮ።
ያለአንዳች ፍርሐት እንዲሠራ
በመሰለው ሞያ ሲሰማራ፣
የአዕምሮ ገደብ ሲወገድ
መጻፍ መናገር ሲፈቀድ፣
ማመቻቸት ሁሉን በሚዛናዊ አሠራር
ፍትሕ መስጠት መሥራት ማሠራት
ማስተማር
ያለምንም አድልዎ መልካም ተግባር፣
ወንድማማችነት ሲጎለብት ጥላቻ ፍጹም
እንዲጠፋ
መተባበር መተጋገዝ መከባበር ሲሰፋ፣
ቋንቋ ዘር ሃይማኖት ጎሳና ፆታ
ሳይወስነው
የሰዎችን እንቅስቃሴ ምንም ሥልጣን
ሳይገድበው።
ለግሉ ሳይሆን ለትውልድ የሚያስብ ዜጋ
ተፈጥሮ
በንግግር ሳይሆን ሞያ በተግባር ተዘክሮ፣
ሁሉም እንደሠራው መጠን በትክክል
ሲከፈለው
ለአገልግሎቱ የሚመጥን ታዋቂነት
ሲሰጠው።

ወይስ ምላሱ ተቆርጦ በሬው
መብላት አቅቶት ጉሮሮው ቆስሎ ሲሞት
ሚስቱን ተቀምቶ ገበሬው፣
መሬት ሃብት ንብረት ተዘርፎ
ለማይጠቅም ገቢ
የመንግሥት ሐራጅ ቅርጫ ተሰልፎ፣
ቤት ለማፍረስ ጣራ መገንጠል
ሃብት ንብረትን ጋዝ ለኩሶ ማቃጠል፣
የፍራሽ ሥራ ላብአደር ሂሳብ ማስከፈል
የዕርዳታ እህልና የባንክ ብድር
ማስከልከል፣
ከኤድስ መድኃኒት ተጠቃሚነት
ማስወገድ
ያለውዴታ አልተፈቀደ ምዝገባ
ማስገደድ።

የውሸት ወንጀል ፈጥሮ ማሰር
ለመኸር ተፈላጊ የእህል ዘር
ማዳበሪያ ከልክሎ ጦም ማሳደር፣
ከማኅበራዊ ተሳትፎ ማስሰረዝ
እንቅፋት መፍጠርና የኑሮ ተስፋን
ማደንገዝ፣
ነጋ ጠባ ሰዎችን ማሰቃየትና መቀጥቀጥ
ችግር ማባባስና የወገንን ሞራል ማዝቀጥ፣
የቱ ነው ትክክሉ
ለእኔስ የሚመስለኝ
ምነው ወደ ጥሩ ብናመራ
ደግ ደጉን ብንሠራ
መልካም መልካሙን ብናወራ።

ዓለማየሁ አስፋው/ ቶሮንቶ